# ስብሰባና ሀበሻ

## ስብሰባ

የዛሬውን አያድርገውና ስብሰባ አለ ካሉኝ ጊዜው ደርሶ ወደ ስብሰባው እስከምሄድ እንቅልፍ ይነሳኝ ነበር።ለእኔ ዋናው ቁም ነገሩ ተቃዋሚዎች ስብሰባውን መጥራታቸው ስለሆነ ስብሰባው ስለምን እንደሆነ ወይም የትኛው ድርጅት እንደጠራው አልጠይቅም ።መአሕድ ይሁን መድን፣ኢሕአፓ ይሁን ደቡብ ሕዝብ፣አማራጭ ምክር ቤት ይሁን ኦብኮ፣ሠራተኛ ማህበር ይሁን መምህራን ማህበር ሁል ግዜ እሳተፋለሁ።እናት ሃገራችንን ከገባችበት የወያኔ ዘረኛ አስተዳደር ለማውጣት በሚደረግ ትግል በተቻለኝ ሁሉ አስተዋፅኦ ለማድረግ ጥረት አደርግ ነበር። ወያኔን የሚታገሉት ሁሉ በጠሩት ስብሰባ ላይ መገኘትና ማበረታታት ግዴታዬ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር። የስብሰባው ግዜ ደርሶ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ተገናኝቼ ለመወያየት ችኮላዬ አይጣል ነው። እንዲያውም ቀደም ብዬ ሄጄ ከሌሎች ከማውቃቸው ጋር መወያየትን አዘወትራለሁ።አዳራሹ ሲከፈት የተጠየቅሁትን ከፍዬ እገባለሁ።ውስጥም የገንዘብ መዋጮ በሚጠየቅበት ጊዜ ያለኝን እሰጣለሁ።

በወቅቱ የድርጅት መሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች ፣ አርቲስቶች ፣ "ሀገር ወዳዶች" እየተጋበዙ የሚመጡበት ዘመን ነበር። አንዳንዶቹን ለስብሰባ የተጋበዙትን ግለሰቦችን አንዴ ሳይሆን ብዙ ግዜ ሰምቻቸዋለሁ።ተስፋ አልቆርጥም አዲስ ነገር ያመጡ ይሆን?የዛን ሕዝብ ስቃይ ያቆሙ ይሆን? በሚል ደጋግሜ እሄድ ነበር። ለምሳሌ በየነ ጴጥሮስ፣ ልደቱ፣ መረራ ጉዲና፣ ፕሮፌስር መስፍን ፣ጉሹ ወልዴ ፣ ነገደ ጎበዜ፣ አረጋዊ በርሄ፣ ወዘተ ከአንድ ግዜ በላይ ሰምቻቸዋለሁ።

ለስብሰባ ተጠርተው ስለትግሉ ብዙ ከቀሰቀሱን በኋላና እኛም ሄደው ወያኔን ጉድ አፈሉበት ብለን ስናስብ የተሰበሰበውን ገንዘብ ይዘው ጥገኝነት ጠይቀው እዚሁ የቀሩም ብዙ ናቸው።አትሂድ ብለን ለምነነው አይሆንም ብሎ ሄዶ ለብዙ ዓመታት የታሰረም እንደ ዶክተር ታዬም ዓይነት አለ። ስብሰባ ብዙ ሰው አስተዋውቆናል። ማስተዋወቅ ብቻ አይደለም ብዙም አስተዛዝቦናል።

ግለሰቦች በተለያየ ድርጅት ሊቀመንበርነት ስብሰባ ሲጠሩ ተገኝቻለሁ።ለምሳሌ በየነ ጴጥሮስን እንመልከት። በደቡብ ሕዝቦች ሊቀመንበርነት ፣ በአማራጭ ሃይሎች ሊቀመንበርነት፣ኅብረት ሊቀመንበርነት ወዘተ ። አሁን ደግሞ በወያኔ ፓርላማ ውስጥ የሕዝብን ተቃውሞ ወደ ጎን በመተው ይገኛሉ። አዲስ አንቀፅ 39 በመደገፍ በተቋቋመው መድረክ በሚባለው ህብረትም ብቅ ብለዋል።

እነዚህ ዓይነት ግለሰቦች በመጀመሪያው ሊቀመንበርነታቸው ምንም እንዳልሰሩ ሳውቅ በሁለተኛው ምን እንደምጠብቅ አላውቅም ግን ስብሰባው ሲጠራ እሄዳለሁ። የሚገርመው የእኔ መሄድ ሳይሆን እየደጋገሙ ሌላ ግለሰብ እንደሌለ እነዚሁኑ ግለሰቦች በሊቀመንበርነት የሚመርጡት ናቸው።እነዚህ ግለሰቦች ትግሉን ምን ያህል እንደጎዱት የሚታወቅ ነው። በመስተጨረሻው ክህደታቸውን አይተናል። በሚቀጥለውም ቢመጡ እንደምንቀበላቸው እየተቀሰቀስን ነው።

እኔ እንደ ፆታ መቀየር የሚስፈራኝን የአቋም መቀያየር ጉዳይ አንዳንዶቹ የወቅቱ እንግዶች በየግዜው ያደርጉታል።በተለያየ ጊዜ የተለያየ አቋም ይዘው ንግግር ሲደርጉም ተመልክቻለሁ። በተወሰነ ወቅት ካለ መሳሪያ ትግል ወያኔ አይወርድም ብሎ ሲቀሰቅስ የነበረ፣ ከረም ብሎ ደግሞ የሰላም ትግል ነጭ ርግብ በእጄ ይዣለሁ ብሎ ሲቀሰቅስም የሰማሁት አለ።ይህ ማለት ደግሞ ፈረሱን ከጋሪው ማስቀደም ነው። ለመሳሪያ ትግል ያዋጣነውን ገንዘብ የት እንደደረሰ ሳይነግሩን ለሰላም ትግሉ እንድናዋጣ ሲጠይቁን ምንም ሃፍረት አይሰማቸውም።

አሁንም ሌላ ሕብርት ቢፈጠር እነዚህን ሊቀመንበሮች ፣ እነዚህን ኮሚኮች ፣እነዚህ "አገር ወዳዶች"፣ እነዚህ አንዴ የመሳሪያ ፣ አንዴ ደግሞ የሰላም ታጋዮች እንደገና እንደምናገኛቸው አልጠራጠርም። የተለመደ ነውና እንደገናም ስብሰባ እንጠራ ይሆናል፡፡ አሁን ግን ግዜው ተሻሽሏል። በጠዋት መውጣት የለም፣ ገንዘብ መክፍል የለም፣ አውቶቡስና ባቡር መጠበቅ ቀርቷል፣ሁሉም ነገር ቀላል ሁኗል።ፓልቶክ ሁሉንም ገላግሎናል።እቤታችን ቁጭ ብለን ሁሉንም እሰማለን።

በተለያየ አቋም ከተመላለሱት ስም ከተመላለሱት ከሁሉ የሚገርመኝና የሚያስቀኝ ደበበ እሸቱ ነው። በፖለቲካ ለመጀመሪያ ግዜ ያየሁት የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት ግዜ ወያኔን ወክሎ መጥቶ ነው።ይህ አርቲስት ወያኔን እንደ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሲቀሰቅስን ይንዘፈዘፍ ነበር። ይህ ወቅት በወያኔ ላይ የነበረው ተቃውሞ የጦፈበት ቢሆንም ለደበበ ያ አልታየውም። ትዝብት ነው።

ከዛም ተቃዋሚ ሆኖ በቅንጅት ግዜ ተመልሶ መጣ።ቅንጅት ሲፈርስ የአንደነት ፓርቲን ወከለ። እንደገና ደግሞ በሚቀጥለው ግዜ በምን ተወክሎ እንደማየው አለውቅም። ሂደቱ ከወያኔ ይመስላል።መድረክን ወክሎ አንቀፅ 39 እንድንቀበል ሊቀሰቅሰን ይመጣ ይሆናል።ባለፈው ሳምንት በድኅረ ገፆች ላይ እንዳየነው ደግሞ ሲጣላ ያየነው ነው።ግለሰቡ ባለው የፖለቲካ ማይምነት ባሻገር ደግሞ አቋሙን ሲቀያይር ፈጣን ነው።

ስለ ደበበ እሸቱ ሳነሳ ሌላ የአቋም መቀያየር በግሌ የደረሰብኝን ላጫውታችሁ።

## ሀበሻ ነህ ወይ ?

ወያኔ ስልጣን ላይ እንደወጣ በውጭ ሀገር የሚገኙ የትግራይና የኤርትራ ልጆች ፍቅር ጦፎ ነበር። ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ፣ ወያኔ ከሻቢያ ሲጣል፣ የኢትዮጵያ ልጆች ሻብያ በቀበረው ፈንጂ ላይ ሲማገዱ ፣ ሻቢያ ትግራይ ክፍለ ሀገር በአውሮፕላን ሲደበድብ ፣ ያ ሁሉ መዐት ሲደርስ፣ የትግራይ ልጆች የሌላውን የኢትዮጵያ ክፍል እርዳታ በጣም በሚፈልጉበት ጊዜ ፣ አይናችሁን አንይ ያሉንን እትዮጵያውያን ፍለጋ ጀምረው ነበር። በዚያ ወቅት አንድ የማውቀው የትግራይ ተወላጅ አግኝቼው ነበር።ታዲያ ይህንን ግለሰብ ከአንድም ሁለት ሦስቴ በተለያ አቋም አግኝቸዋለሁ። እሰቲ ሁኔታውን ላጫውታችሁ።

አሁን ወደ እምኖርበት አገር ስመጣ ምን እንደሚጠብቀኝ አላውቅም ነበር። ገና ወያኔ ስልጣን ላይ በወጣ በወሩ አካባቢ ነው። ሁሉም ነገር ግራ የሚያጋባ ወቅት ነበር። እዚህ ሀገር ከመምጣቴ በፊት የነበርኩበት ሀገር ትምህርት ላይ በነበርኩበት ወቅት ስለወያኔ ሁኔታ ስብሰባ ይደረግ ነበር።ወያኔን በሚመለከት ብዙ ብዙ የማውቀውን ተናግሬ ስለ ነበርና ወደ ሀገሬ ከመመለስና ያ ጥንት የቀመስኩትን ስቃይ ከመድገም ብዬ ላልመመለስ ወስኜ ነበር የመጣሁት።ስደት ምን ይመስላል? ብባል ምንም አላውቅም። ጉዞዬ የምዕራብያውያንን ዴሞክራሲን ተማምኜ፣ የእነርሱን ሃብት ልካፈል ነበር።ገና ከመጀመሪያው ቀን ነበር መራራውን ሀቅ መጠጣት የጀመርኩት።

ከባቡር የወረድኩበት ከተማ ትርምሱ ብዙ ነበር። አማራጭ ስላልነበረን የሃገር ልጅ መፈለግ ጀመርኩ።
-መጀመሪያ ያገኘሁትን ሰላም አልኩት።
-አስላመት አለኝ ።
-ቀጠልኩና ኢትዮጵያዊ ነህ አልኩት።

ምንም መልስ ሳይሰጠኝ ገላምጦኝ ሄደ። ደነገጥኩ።አንድ ነገር እንደተሳሳትኩ ገባኝ።ምን ነገር አስቀየምኩት ብዬ እንደገና ሌላ ሰው ለመጠየቅ ፍርሃት አደረብኝ። ከዛም አለፍ አለፍ እያሉ የሚመጡትን ጠያይም እኔን የሚመስሉ ሰዎችን ዝም ብዬ አሳልፍ ጀመርኩ። ከብዙ ግዜ ቆይታ በኋላ አንዷ ብቻዋን ስትመጣ አየኋትና፣

- ኢትዮጵያዊ ነሽ? ብዬ ጠየቅኋት።
- አምሃራይ ብላኝ እየሳቀች ጥላኝ ሄደች።

አሁን በጣም ግራ ተጋባሁ። የመጀመሪው ገላምጦኝ ሄደ፣ የአሁኗ ደግሞ አማህራይ ብላ ስቃ ሄደች። የመጀመሪያውን ምን እንዳስቀጣውም ወይም የሁተኛዋን ምን እንዳሳቃት ስላልገባኝ ግራ ገባኝ። አሁን መጠንቀቅ እንዳለብኝ ተረዳሁ። ዝም ብዬ አካባቢውን አጠና ጀመር።ለካ አላወቅሁትም እንጂ ይህ የፈረንጅ ከተማ እንደ ናቅፋ ቀደም ብሎ በሻብያ ነፃ የወጣ ነበር።ኢትዮጵያዊ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ተረዳሁ።እነርሱን ኢትዮጵያዊ ነህ ወይ ብሎ መጠየቅ እንደ ስድብ እንደሚቆጥሩት አልገባኝም ነበር። የመጀመሪያው ትምህርቴ እሱ ነበር። ይህንንም ትምህርር ያገኘሁት እንደዚሁ ስፈራ ስቸር ከጠየቅሁት ግለሰብ ነው።

-ስላም አልኩትና ጥያቄውን አዘገየሁ።
-ታዲያስ አለኝ።
-አለን አልኩት።
-አዲስ ነሽ መሰለኝ አለኝ።
-እኔን የሚክል ግብዳ ሰው አንቺ ሲለኝ ግራ ቢገባኝም አዎ አዲስ ነኝ አንተስ? ብዬ ጠየቅሁት።
-ትንሽ ቄይቻለሁ። አንድ አራት አመት ሆኖኛል።
-እኔ ዛሬ መምጣቴ ነው። ብዬ ቀጠልኩ።
-ኢትዮጵያዊ ነህ ኤርትራዊ? ብሎ ጠየቀኝ።
-ኢትዮጵያዊ ወይስ ኤርትራዊ? የሚለው መጀመሪያ ጊዜ መስማቴ ስለነበር ደነገጥኩ።ኢትዮጵያዊ ነኝ ብዬ መለስኩለት።
-እጅሽን ልትሰጪ ነው እንዴ? አለኝ።

-አሁንም አንቺ የሚለው ንግግር እየሰቀቀኝ፣ በዛ ላይ እጅ መስጠት የሚለው ቃል ለወንጀለኞች ነው፣ በሚል እየጨፈገገኝ፣ አዎ ጥገኝነት ልጠይቅ ነው። ግን እዚህ ማንንም አላውቅም። እንዴትና ወዴት እንደሚጠየቅ ብትረዳኝ አልኩት።

-ቀላል ነው ኬዝ አዘጋጂና ሄደሽ እጂሽን መስጠት ነው አለኝ።

-ቦታውን ታሳየኛለህ? ብዬ ጠየቅሁት።

-ሽቀላ ልሄድ ነው አሁን አይመቸኝም ነገ ከፈለግሽ እዚህ ጋ ጠብቂኝና እረዳሻለሁ አለኝ።

-ለማንኛውም በስንት ሰዓት ብዬ ጠየቅሁት ?

-አስራ ሁለት አለኝ።

-በየትኛው አቆጣጠር? ብዬ ለመጠየቅ ስዘጋጅ ቻው ብሎኝ እየበረረ ሄደ።

-ተመልሼ የነበርኩበት ቦታ ላይ ቆምኩ። አንድ የተማርኩት ነገር ቢኖር ኢትዮጵያዊና ኤርትራዊ የሚለውን ብቻ ነው። ዘመን እንዳለፈ ገባኝ።ኢትዮጵያ አንድነት ከሥሩ እንደተናጋም ታሰበኝ።ዐይኖቼ እንባ አቀረሩ። ተሸናፊነት ተሰማኝ። ደከመኝ።በአንድ በኩል ደግሞ ቢሆንም ባይሆንም ይህንን ችግሬን የሚካፈልልኝ ኢትዮጵያዊ ማግኘት ናፈቀኝ።

እንደገና መጠበቅ ጀመርኩ። መጠበቅ ። መጠበቅ ። የሚቀጥለውን እንዴት እንደምጠይቀው ማሰብ ጀመርኩ። ኤርትራዊ ነህ? እንዲህ ብሎ መጠየቅ አገሬን እኔው እራሴ እንድትበጣጠስ የረዳሁ መሰለኝ። ሰዓቱም ደግሞ እየበረረ ነው። ምን ልበል? መጠበቅ ጀመርኩ። አንድ እንደ ሌሎቹ ፀጉሩን ያላጎፈረ ብቻው ሲመጣ አግኝቼ ይህ ኢትዮጵያ ሳይሆን አይቀርም ብዬ ሰላም አልኩት።

-ንህዳ አለኝ?

-አለና አልኩ እኔም።ሳድሱን በእራብእ ቀየርኩና ትግሪኛ አደረግሁት።

-ከመይ አልኝ?

-ፅቡቅ አልኩ ።

-የአዲስ አባባ የጎረቤታችን የአዴይ ትግሪኛ በጣም እረዳችኝ።

-አማህራይ ዲዩ? አለኝ ።

-እወ አልኩ።

-ጠብቀኝ አለኝና ሄደ።

ተመልሶ ከሌላ አንድ ሰው ጋር መጣና ሰውዬውን አገናኝቶኝ እሱ ይረዳሃል ብሎ ቻው ብሎኝ ሄደ።አዲስ የመጣው ሰው አዲስ መምጣቴንና ምን እንደምፈልግ በቀለጠፈ አማርኛ ጠየቀኝ።ጥገኝነት እንደምፈልግ ነገርኩት። በጣም ተናደደ።ይጮህ ጀመር። ደርግ እንደወረደና ዴሞክራሲ እንደተስፋፋ ነገረኝ።የአማራ ትምክኽተኛ ካልሆንኩ፣የኢሠፓ አባል ካልሆንኩ፣ወንጀል ከሌለብኝ፣ ተመልሼ ወደ ሃገሬ መሄድ እንደለብኝ አስረዳኝ።ወንጀል ካለብኝ ግን የዚህ ሀገር መንግስት አንጠልጥሎ ለወያኔ እንደሚሰጠኝ አስፈራራኝ።በጩኸቱ ብዛት ሌሎችም “ኤርትራውያን“ ከበቡኝ ።እንደገባኝ በኋላም እንዳወቅሁት ለካ አዲስ የመጣው የትግራይ ልጅ ነው።እኔን በመስደብ ታማኝነቱን ለኤርትራውያኑ አሳያቸው።የኤርትራም የትግራይም ልጆች አንድ ላይ አበሩብኝ።አዋከቡኝና ጥለውኝ እየተሳሳቁ በትግሪኛ እያወሩ ሄዱ።ተመልሼ ብቸኛ ሆንኩ።ትግራይም አብራ የተገነጠለች ይመስል ከልቤ ሀዘን ገባኝ። ደነገጥኩ። ብቸኝነት ተሰማኝ። ያ ሳቃቸው እስከ አሁን ድረስ ይሰማኛል።ግን ልቦናዬ ይህ ቅጥ ያጣ ፍቅር ዘላለማዊ እንዳልሆነ ይነግረኝ ነበር።

ከኤርትራዎቹ አንዱ ተመልሶ በተሰባበረ አማርኛ አንድ የአማህራይ ቡና ቤት አለ እዚያ ሂድ ብሎ መከረኝ። ቦታውን አላውቀውም አልኩትና አሳየኝ ።ከሃገሬ ልጆች ተገናኝቼ ህይወት ቀጠለች። ከብዙ ግዜ በኋላ ያንን የትግራዩን ሰው በሌሎች አጋጣሚዎች አገኘሁት።

በመጀመሪያ ጊዜ እኔ የምሰራበት መስሪያ ቤት ለመቀጠር መጥቶ እኔ ቀጣሪ እሱ ተቀጣሪ ሆኖ ተገናኘን።ገና ሲያኝ ደነገጠ። ያ መንገድ ላይ ጥሎት የሄደው ግለሰብ ቀጣሪ ፣ እሱ ደግሞ ተቀጣሪ ሆኖ ማየትን ትምክህተኛ ልቡ፣ ዘረኛ መንፈሱ አልተቀበለውም።ውርደት ተሰማው። በኢሠፓም ፣ በአማራም ፣ ሊያሳብብ አልቻለም። የአበላለጠን እውቀትና ችሎታ ነው። አንቀፅ 39 አይደለም። ክልልም አይደለም። በእኔ መቀጠር ውርደት መስሎት ወረቀቱን እንድንመልስለት ጠይቆ ሄደ።እውነቱን ለመናገር በዚህ ወቅት በዚህ ግለሰብ ላይ ምንም ቂም አልነበረብኝም። እማይለመድ ነገር የለምና ሁሉንም ለምጄው ነበር።ኤርትራዊ የሚለውን ቃል ከፈረንጆቹም ሳይቀር ሰምቸዋለሁ።አገሩንም ሕዝቡንም አውቄዋለሁ። የኢትዮጵያውያንም ቁጥር ጨምሮአል።

ከዛ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ የተገናኘነው ደግሞ እነ ደበበ እሸቱ ስለ ኤርትራና ኢትዮጵያ ጦርነት የተዘጋጀው ዝግጅት ላይ ወያኔን ወክለው በመጡ ወቅት ነው። አሁን ይህ ግለሰብ አቋሙን ቀይሮ ኢትዮጵያውነትን አጥብቆ በፈገግታ ተቀበለኝ።የድሮውን ነገር እሱ የረሳው መስሎ ቀረበኝ። ካለ ምንም ይሉኝታ ከእኔ በላይ ኢትዮጵያዊ ሆኖ የሃገርን ጠላት አብሮ ተባብሮ መዋጋት እንደሚያስፈልግና ታላላቅ አርቲስቶች እንኳ ከወያኔ ጋር እንደሚሰሩ ወደ ደበበ እሸቱ እየጠቀሰ አስረዳኝ።እኔም ይሁና ብዬ ዝም አልኩት።የወያኔን ዴሞክራቲክነት፣ ወያኔ ከሻቢያ ከተጣላ ብዙ ለሃገሪቱ እንደሚሰራ አስረዳኝ። እፍረት ይዞት ብዙ ቀባጠረ እንጂ እንዲህ በቀላል እጄን እንደማልሰጥ ተረድቶታል።

በዚህ ወቅት ነበር ብዙ "ሃገር ወዳዶች" ሁኔታውን ተጠቅመው ወደ ወያኔ የገቡት።ታቃዋሚ ድርጅቶችን ዓይናቸውን አንይ ያሉት። የታወቁ የወያኔ ተቃዋሚዎች የነበሩ ግለሰቦች ወያኔን መደገፍ ጀመሩ።አዲስ ሙሉ ልብስና ከረባት እየገዙ ወደ አዲስ አበባ ተጓዙ።የኢትዮጵያ ድንበር ቀይ ባህር መሆኑ ቀርቶ ባድሜ መሆኑን አመኑ። ከሁሉ የሚገርመኝ ሻለቃና ሻንበል የነበሩ መለዮ ለባሾች ይህንን አምነው መቀበላቸው ነው።በዛን ጊዜ የተወሰኑ ግለሰቦች የተለየ ሃሳብ ቢያቀርቡ ማንም ሊቀበላቸው አልቻለም። አቋም እንደ ሸቀጥ ተቀየረ።

ያ ስብሰባ ለእኔ ደግሞ የመጨረሻዬ ሆነ። ቁንጮ ቁንጮ የሆኑ ተቃዋሚዎች ጦርነቱን ደገፉ። የሚያሳዝን ሁኔታ ደረሰ። የወያኔ ግፍ ተረሳ። አሮጌ ቅራኔ በአዲስ ተተካ። እንደ ቀድሞ ስብሰባ ወግ አጣ። የወያኔ ካድሬዎቻና እኛ አብረን ቆረስን። ከዛ በኋላ የምሄድበትን ስብሰባ መምረጥ ጀመርኩ።

ለሶስተኛ ጊዜ ያንን የትግራይ ግለሰብ ያገኘሁት በከተማው በሚገኘው ቡና ቤት ውስጥ ነው። የዚህ ቡና ቤት ባለቤት ሌላ የሚቀያየር አቋም ያለው ነው።የባለቤቱ አቋም ቡና ቤት ውስጥ ሊጠጣ በመጣው እንግዳ ይወሰናል።ተቃዋሚዎች ሲሄዱ የተቃዋሚዎችን አቋም ይይዛል። የተቃዋሚዎች ጋዜጣ ይሰጣል።ወያኔዎች ሲመጡ ደግሞ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ያወጣል።አቋሙ እንደ ገበያው ይቀያየራል። የተቃዋሚ ድርጅቶችን ወረቀት በመስጠት የተቃዋሚዎችን ደንበኝነት ይፈልጋል። አዲስ ዘመንን በመስጠት ደግሞ ከወያኔ በርበሬንና ቅቤውን ያገኛል።እዚህ ቡና ቤት ነው ለሶስተኛ ግዜ ያንን የትግራይ ግለሰብ ያገኘሁት።

አሁን ደግሞ አቋሙን ቀይሯል። መለስ ዴሞክራቲክ እንዳልሆነና አምባገነን እንደሆነ፣ እነ ስዬ ከመለስ እንደሚሻሉ አስረዳኝ። ተቃዋሚዎቻቸው አንድ ላይ መስራት የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑን ገለፀልኝ።ስለ አሰብ ወደብ የኢኮኖሚ ጥቅም አስረዳኝ። እኔ ከቆምኩበት ሳልመለስ እሱ ሄዶ በተመለስ እኔን እንደገና ያስረዳኝ ጀመር። ከውይይታቸን እንደተረዳሁት አሁንም ቢሆን የቀመሰው የዘር አብሾ አለቀቀውም። በሚቀጥለው ይህ ግለሰብ የአረና የነ ገብሩ አስራት ድርጅት ተወካይ ሆኖ ስብሰባ ይጠራን ይሆናል። ማን ያውቃል።

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ያ በጣም ችግር ውስጥ የከተተኝ "ኢትዮጵያዊ ነህ ?" የሚለው ጥያቄ መፍትሄ ተገኘለት።በአዲስ ቃል ተቀየረ። " አበሻ ነህ?" በሚል ተተካ። እኛም መሳቀቃችንን አቆምን።" ሀበሻ ነህ ወይ? „ የሚል አባባል ሁላችንንም አስማማን። ኢትዮጵያዊ ነህ ወይ የሚለውን በወያኔ የዘር ፖለቲካ "ሃበሻ ነህ ወይ" ? የሚለው ተካው። ለእኔ ኢትዮጵያዊ ነህ የሚለው እንደጣፈጠኝ ቀረ።

ለወያኔና ለዘረኞች በሙሉ ግን አሁንም ወደፊትም ኢትዮጵያዊነት ሬት ነው።

ኢትዮጵያዊነት ለዘላለም ይኑር ።
በልጅግ አሊ